## በቅማል ህክምና እና መከላከል ላይ የወላድጅ ወይም የአሳዳጊ ሃላፊነቶች

_______ልጅዎ ቅማል እንዳለው ተስተውሏል። ቅማልን በማከም እና ቅማሉ ተመልሶ እንዳይመጣ በመከላከል ረገድ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ጠቃሚ ሚና አላቸው። በ FCHD ድረገፅ https://www.fairfaxcounty.gov/health/schools ላይ የሚገኘውን የቅማል መግለጫ ለማግኘት ብሮሽሩን ይመልከቱ

_______ማሳከክ የመሳሰሉ የቅማል መኖር ምልክቶች ባይኖሯቸውም እንኳን፣ በቤተሰቡ ውስጥ ያሉትን ማንኛውም ሰዎች ፀጉር ይፈትሹ። እርስዎንም የሆነው ሰው እንዲፈትሽዎት ያድርጉ!

_______በፌደራል የምግብ እና መድሃኒት አስተዳደር (FDA)-በጸደቀው ጸረ-ቅማል ህክምና ቅማል ለያዛቸው ሰዎች ብቻ ጥቅም ላይ መዋል አለበት። ከሁለት ዓመት በታች ለሆኑ ህጻናት እና ነፍሰጡር ለሆኑ ወይም ጡት ለሚያጠቡ ሴቶች፣ ለህክምና ምክር እባክዎ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያማክሩ።

_______ከመጀመሪያው ህክምና በኋላ፣ ከትምህርት ቤቱ የጤና ክፍል የቅማል ህክምና ማረጋገጫ ቅጽን ይሙሉ። ወደ ትምህርት ቤቱ በሚመለሱበት ጊዜ ቅጹን ለልጅዎ የትምህርት ቤት ጤና ክፍል ይመልሱ።

_______የልጅዎ የቅርብ ግንኙነት ለነበራቸው ሰዎች ወላጅ/አሳዳጊ ልጅዎ ቅማል እንዳለበት ያሳውቁ።

_______ልብሶች፣ አልጋ ልብስ፣ እና ለስላሳ እቃቃዎችን ሙቅ ዉሃ እና ሙቅ ማድረቂያ በመጠቀም (ቢያንስ ለ 20 ደቂቃ) ያጽዱ። መታጠብ የማይችሉ እቃዎች በፕላስቲክ ቦርሳ ለ 14 ቀናት መታሸግ አለባቸው።

_______ምንጣፍ፣ መጋረጃ እና የመኪና ወንበሮችን በቫኪዩም ማጽዳት። ቤትዎ ውስጥ ማንኛውንም ጸረ ተባይ መድሃኒቶች አይጠቀሙ።

_______ቤትዎ ውስጥ ያሉ ሁሉም ማበጠሪያዎች እና ብሩሾች ላይ መድሃኒት ይርጩ እንዲሁም በየቀኑ በሙቅ ዉሃ ይጠቡ። መድሃኒት መርጨት የሚከናወነው ማበጠሪያዎችን እና ብሩሾችን በ FDA-በጸደቀው የጸረ-ቅማል ሻምፖ ለ 1 ሰዓት መዘፍዘፍ ወይም ከ 5-10 ደቂቃ በዉሃ ውስጥ በመዘፍዘፍ ነው።

_______ከመጀመሪያው ህክምና በኋላ ሳጥኑ ወይም ምልክቱ ላይ ባሉት መመሪያዎች መሰረት ልጅዎን እንደገና ያክሙ። ለልጅዎ የትምህርት ቤቱ ጤና ክፍል ሁለተኛውን የቅማል ህክምና ማረጋገጫ ቅጽ ይመልሱ።

_______ከመጀመሪያው ህክምና በኋላ **በየቀኑ** ለ 14 ቀናት ቅጫሞችን ለማስወገድ የልጅዎን ፀጉር በቅማል እንቁላል (ቅጫም) ማበጠሪያ ይፈትሹ እንዲሁም ያበጥሩ።

_______የልጅዎን ጭንቅላት ቢያንስ ለ 2-3 ሳምንታት በየ 2-3 ቀናት መፈተሽ ይቀጥሉ።

_______ሁሉንም ደረጃዎች ተከትለው ልጅዎ አሁንም ቅማል ካለው ምክር ለማግኘት የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ።

_______ሁሉንም የህክምና ደረጃዎች ለመከተል የቅማል ህክምና የቀን መቁጠሪያን ይጠቀሙ።

# የቅማል ህክምና የቀን መቁጠሪያ

| ቀን 1 | ቀን 2 | ቀን 3 | ቀን 4 | ቀን 5 | ቀን 6 | ቀን 7 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. በ FDA-የጸደቀ የጸረ-ቅማል ህክምናን ይጠቀሙ። የምርቱ ምልክት ላይ ያሉትን መመሪያዎች በትክክል ይከትሉ።<br><br>2. ልብሶች፣ የአልጋ ልብሶች እና ለስላሳ እቃቃዎችን ይጠቡ። መታጠብ የማይችሉ እቃዎችን በፕላስቲክ ቦርሳ ለ 14 ቀናት አሽገው ያስቀምጡ።<br><br>3. የቅርብ ንክኪ የነበራቸውን ሰዎች ያሳውቁ።<br><br>4. ከልጅዎ የትምህርት ቤቱ ጤና ክፍል የቅማል ህክምና ማረጋገጫ ቅጽ ይውሰዱ። ህክምናው ከተጠናቀቀ በኋላ ቅጹን ይሙሉ። | ለልጅዎ የትምህርት ቤቱ ጤና ክፍል የተሞላውን የቅማል ህክምና ማረጋገጫ ቅጽ ይመልሱ።<br><br>የልጅዎን ፀጉር በማንኛውም ዓይነት ሻምፖ አይጠቡ።<br><br>የልጅዎን ፀጉር በዉሃ ያርጥቡ እንዲሁም ወደ ትንንሽ ክፍሎች ፀጉሩን ይከፋፍሉ። የቅማል እንቁላል (ቅጫም) ማበጠሪያ ይጠቀሙ እኒድሁም የልጅዎን ሙሉ ራስ ያበጥሩ። | የልጅዎን ፀጉር ለማጠብ መደበኛ ሻምፖ ይጠቀሙ።<br><br>የትናንትናውን መመሪያ ይከተሉ እንዲሁም የልጁን ፀጉር በቅጫም ማበጠሪያ ያበጥሩ። | የልጅዎን ፀጉር ለማጠብ መደበኛ ሻምፖ ይጠቀሙ።<br><br>የልጁን ፀጉር በቅጫም ማበጠሪያ ያበጥሩ። | የልጅዎን ፀጉር ለማጠብ መደበኛ ሻምፖ ይጠቀሙ።<br><br>የልጁን ፀጉር በቅጫም ማበጠሪያ ያበጥሩ። | የልጅዎን ፀጉር ለማጠብ መደበኛ ሻምፖ ይጠቀሙ።<br><br>የልጁን ፀጉር በቅጫም ማበጠሪያ ያበጥሩ። | የልጅዎን ፀጉር ለማጠብ መደበኛ ሻምፖ ይጠቀሙ።<br><br>የልጁን ፀጉር በቅጫም ማበጠሪያ ያበጥሩ። |

| ቀን 8 | ቀን 9 | ቀን 10 | ቀን 11 | ቀን 12 | Day 13 | ቀን 14 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የልጅዎን ፀጉር ለማጠብ መደበኛ ሻምፖ ይጠቀሙ።<br><br>የልጁን ፀጉር በቅጫም ማበጠሪያ ያበጥሩ።<br><br>። | **ከመጀመሪያው ህክምና ከ 9-10 ቀናት በኋላ፣ ወይም በሳጥኑ ወይም ምልክቱ ላይ ባለው መመሪያ መሰረት፣ ልጅዎን ለሁለተኛ ጊዜ በ FDA-በጸደቀው የጸረ-ቅማል ህክምና ያክሙ።**<br><br>የልጁን ፀጉር በቅጫም ማበጠሪያ ያበጥሩ። | ለልጅዎ ትምህርት ቤት የተሞላውን የቅማል ህክምና ማረጋገጫ ቅጽ ይመልሱ።<br><br>የልጅዎን ፀጉር በማንኛውም ዓይነት ሻምፖ አይጠቡ።<br><br>የልጁን ፀጉር በቅጫም ማበጠሪያ ያበጥሩ። | የልጅዎን ፀጉር ለማጠብ መደበኛ ሻምፖ ይጠቀሙ።<br><br>የልጁን ፀጉር በቅጫም ማበጠሪያ ያበጥሩ። | የልጅዎን ፀጉር ለማጠብ መደበኛ ሻምፖ ይጠቀሙ።<br><br>የልጁን ፀጉር በቅጫም ማበጠሪያ ያበጥሩ። | የልጅዎን ፀጉር ለማጠብ መደበኛ ሻምፖ ይጠቀሙ።<br><br>የልጁን ፀጉር በቅጫም ማበጠሪያ ያበጥሩ። | የልጅዎን ፀጉር ለማጠብ መደበኛ ሻምፖ ይጠቀሙ።<br><br>የልጁን ፀጉር በቅጫም ማበጠሪያ ያበጥሩ።<br><br>ሁሉንም እነዚህን ደረጃዎች ከተከተሉ በኋላ አሁንም ቅማል ወይም የቅማል እንቁላሎች የሚያዩ ከሆነ፣ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ማነጋገር አለብዎት። |

ተከልሷል፦ ኖቬምበር 2022